## *ብፁዕ አቡነ ብርሃነየሱስ ለ2003 ዓ.ም. የሕሙማን ቀን ያስተላለፉት መልዕክት*

በቅርብም በሩቅም የምትገኙ የክርስቶስን መከራና ሕመም የምትካፈሉ ወገኖቼ በሙሉ :-

*ዳግማዊ ዮሐንስ ጳውሎስ አባታዊ ማሳሰቢያ መሠረት የሕሙማን ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ በወርኃ የካቲት ሲከበር እነሆ 19ኛ ዓመቱን ይዟል። እኛም በሀገራችን ከአዲሱ ሚሌኒየም ዋዜማ ጀምረን በተለያየ ሕመም ከሚሰቃዩት ወገኖቻችን፣ የቅርብ ረዳቶቻቸው፣ የጤና እገዛ ከሚያደረጉላቸው ባለሙያዎችና ለሥጋና ለነፍሳቸው የሚያስፈልጋቸውን የእግዚአብሔርን ፀጋ ከሚያካፍሏቸው ነፍስ አባቶቻቸው ጋር ዘንድሮ ለ5ኛ ጊዜ እናከብረዋለን።*

*ር.ሊ.ጳ. ቤኔዲክቶስ 16ኛ* **በተስፋ** *መዳናችን* **በተሰኘው** *ሐዋርያዊ መልዕክታቸው አንድ ማኅበረሰብ የራሱ የሆኑትን በተለያየ በሽታ ለሚማቅቁትንና ስቃይ ለሚሰማቸው ወገኖቹ ካልራራ እንዴት ጨካኝና ኢ-ሰብዓዊ ነው በማለት ግዴታችንን አስገንዝበውናል* (***Spe Salvi, n.38)***።

*ክርስቶስ ራሱ ሥቃይ በበዛበት ጊዜ የቅርብ ባልንጀሮቹ ጭምር በአጠገቡ አልተገኙም። ለአንድ ሰዓት እንኳ አብረውት መትጋት ተሳናቸው (ማቴ 26)። ምናልባት እኛም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ወገኖቻችን ሲሰቃዩ ከጎናቸው መቆምና የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ከመስጠት ወደኋላ ብለን ይሆናል። ነገር ግን የክርስቶስ ተከታዮች መሆናችን የሚታወቀው እርስ በርሳችን በሚኖረን ፍቅር ነው (ዮሐ 13:35)። አንድ ሰው መከራ በደረሰበት ጊዜ ከጎኑ መቆም፣ ማፅናናትና ማበረታት አይነተኛ ክርስቲያናዊ ምግባር ነው። ሕይወት በእሾክና አሜኬላ የተሞላች ናት። ልጇን ያጣችውን እናት፣ በቀሳፊ በሽታ የተያዘውን ወጣት፣ ከቤት ንብረቱ የተፈናቀለውን ቤተሰብ፣ በጦር ግንባር የቆሰለውን የሠራዊት አባል፣ መንፈሱ ተረብሾ እራሱን ለማጥፋት የሚፈታተነውን ጉብል፣ በሞትና በሕይወት መካከል የሚገኝ ደጋፊ ያጣውን አረጋዊ፣ ያልጋ ቁራኛ ሆኖ የፀሐይ ብርሃን ሳይቀር እንኳ የተነፈገው ሁሉ ..... የኛው ወገን ነውና ጌታችን እንዳስተማረን ከሁሉም ጋር በፍቅር እንተሣሠር።*

*መከራ ሲበዛብን፣ መተማመኛችን ምን እንደሆነና ማን ላይ እንደቆምን እየዘነጋን ተስፋ በመቁረጥ ሕይወት የጨለመ ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን ፊታችንን ወደ እርሱ ከመለስን የህማማቱ ተካፋዮች ለሆንን ሁሉ የትንሣኤው ብርሃን በላያችን ላይ እንደሚያበራ አያጠራጥርም። ሐዋርያዊው ቶማስ ተስፋ ያደረገበት ሁሉ እንዳልነበረ ሲሆን በጥርጣሬ ግራ ተጋብቶ ሳለ የጌታውን ቁስል በጁ ዳስሶ ከጭንቀቱ መፈወሱን ወንጌሉ ይነግረናል (ዮሐ 20)። እንዲሁም የታሠሩበትን ሠንሠለት ፈትቶ ነፃ እንደሚያወጣቸው የተማመኑበት መሢህ ሞቶ የቀረ መስሏቸው ተስፋ የቆረጡት የኤማሁስ መንገደኞች ሥጋውና ደሙን ባርኮ፣ ቀድሶና ቆርሶ ሲሰጣቸው፣ የትንሣኤውን ብርሃን እንደበራላቸው እናውቃለን (ሉቃ 24)።*

ካለብን ሕመም የምንድነው፣ ቁስላችን የሚፈወሰው ለሁላችን የተሠዋው መድኃኔዓለም በሠራቸው ቅዱሳት የቤተክርስቲያን ምሥጢራት በመሆኑ በተለያየ ሕመም የሚሠቃዩት ወገኖቻችን በአግባቡ የትሩፋቱ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ሁኔታዎችን በሙሉ ማመቻቸት እንዳለብን አበክሬ አሳስባለሁ፡፡

የእግዚአብሔር አብ ቡራኬ፣ የእግዚአብሔር ወልድ ፍቅር የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መጽናናት ለሁላችሁ ይድረስ፡፡

የሕሙማን ፈውስ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ ለምኚልን፡፡

+ አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል
ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን
የካቲት 23 ቀን 2003 ዓ.ም